አሁን ወይም በጭራሽ!

ሚያዝያ 8 ቀን 2015 ዓም (16-4-2023)

## ተገንጣዮች የመገንጠል ዓላማችንን ማስፈጸሚያው ጊዜ አሁን ነው (Now or Never)ሲሉ ፣ እኛም የአገራችንን ህልውና ማስከበሪያው ወቅት አሁን ነው(Now or Never)እንላለን!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመብቱና ለፍትሕ ሲታገል ብዙ ዓመታት አልፈዋል።የቀደሙትን የትግል ታሪኮች ስናነሳ ገዝፎ የሚታዪውና የሚታወቀው ከዛሬ 62 ዓመት በፊት የተካሄደው በነጀነራል መንግሥቱ ነዋይ የተመራው ወታደራዊ አመጽ ያካተተ የፖለቲካ ለውጥ ፍለጋ እንቅስቃሴ እንደ መነሻ ብናደርግ ዓላማው በጊዜው ሰፍኖ የኖረውን ዘውዳዊና ባላባታዊ ስርዓት ለመለወጥ ያቀደ ነበር። ለዘመናት ሰፍኖ የኖረው ስርዓት ለአገሪቱ ህልውናና ነጻነት ያበረከተው ድርሻ መኖሩ ባይካድም የሕዝቡ ኑሮና ያገሪቱ እድገት ደረጃ ግን ከኋላ ከተፈጠሩት አገራት በታች መሆኑ የአገር ወዳዱን ልብ የሰበረና ለለውጥ እንዲነሳ ምክንያት ሆኖታል። በተለያዩ ጊዜያት በባላባቶችና በመሳፍንቱ መካከል ግጭት ቢኖርም ለአገር እድገትና ለሕዝቡ ኑሮ መሻሻል ሳይሆን ዋናው ምክንያት የሥልጣን ሽኩቻ ነበር።ያም ሽኩቻ በመደራደር፣ በጋብቻና በሹመት ይወገድ ነበር ።ከዚያ የተለዬው እንቅስቃሴ የ1953ቱ የነጀነራል መንግሥቱ ነዋይ ሲሆን ያም ቢሆን ከክብር ዘበኛ ተቋም አንጻር ሲታይ ጸረ ዘውዳዊ ስርዓት እንዳልነበረ አልጋወራሹን ንጉሰነገሥት አድርጎ የመተካቱ አዝማሚያ ያረጋግጣል። አሁን ላይ ሆነን ስናዬው እንቅስቃሴው ቢሳካ ኖሮ ትንሽ የጥገና ለውጥ ያመጣ እንደሁ እንጂ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣቱ ያጠራጥራል።ቁጥር አንድ የደርግ ዘመን ሊሆን የመቻል ዕድሉ ትልቅ ነበር።ያም ሆነ ይህ ከአድማው ጠንሳሽ ከገርማሜ ነዋይ አስተሳሰብ ስንነሳ የነበረውን ፈላጭ ቆራጭ ዘውዳዊ ስርዓት ሊያለዝበው ይችል እንደነበር ግን አይካድም። ገርማሜ ነዋይ በአሜሪካን አገር የተማሩና የጥቁር አሜሪካውያንን የመብት ትግል በዓይናቸው ያዩ፣ከመሰሎቻቸውም ጋር የተወያዩ በመሆናቸው የሲቪክ መብት ጥያቄን በአግባቡ የተረዱ ነበሩ።አገራቸውም ሲመለሱ የሕዝቡን መብት የማስከበር ትግል በህሊናቸው የተቀረጸው በዚሁ አጋጣሚ እንደነበር የሚያውቋቸው መስክረዋል፣በተመደቡበትም የሥራ መስክ ያረጋገጡት ያንኑ ነበር።ምንም እንኳን ሙከራው በብዙሃኑ የሚደገፍ ቢሆንም የቀሰቀሱት እንቅስቃሴ ግቡን ሳይመታ በሶስት ቀናት ዕድሜ ለመጨናገፍና ተስፋ በመቁረጥ የአገሪቱን ባለሥልጣናት በጅምላ በመጨፍጨፍ የለውጡን መንፈስ በኢሰብአዊነት መድቦ በታሪክ ጥቁር ነጥብ ያሰፈረ እንቅስቃሴ ሆኖ ለመመዝገብ ችሏል።

ለእንቅስቃሴው አለመሳካት በዋናነት ምክንያት የነበረው በቅጡ ባለመደራጀቱና ሕዝቡንም አንቅቶ ያላሳተፈ በመሆኑነው። እንኳንስ ዓላማው ቀርቶ መንቀሳቀሱ በመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይታወቅ በተጀመረ በሶስተኛው ቀኑ ከሸፎ አመጹን የመሩት አገር ወዳዶች እንደ አልባሌ ከሃዲ ተቆጥረው በሙያ አጋራቸው በምድር ጦርና በአዬር ሃይሉ ጦር ሊደመሰሱ ቻሉ። በህይወት የተያዙትም በአደባባይ ተሰቀሉ፤ብዙዎቹም የዕድሜያቸውን ግማሽና እሩብ በእስራትና በግዞት አሳለፉ። እንቅስቃሴው እንደተራ ግርግር ተቆጥሮም እስከአሁን ድረስ የሚታወቀው የታህሳሱ ግርግር በመባል ነው። የእንቅስቃሴው ትርጉምና ምንነት የገባቸው የንቅናቄው መነሻ ከሆነው ቤተመንግሥትና ከክብር ዘበኛ የጦር ሰፈር በቅርብ እርቀት ላይ የሚገኘው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብቻ ነበሩ።እንቅስቃሴው ደግፈው በከሸፈ ማግስት ለመጀመሪያ ጊዜ መሬት ለአራሹ የሚለውን ጥያቄ አደባባይ ይዘው የወጡት እነዚሁ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ነበሩ።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተማሪና ፖለቲካ የማይነጣጠሉ ሆኑ።የተማሪው

እንቅስቃሴ አገር አቀፍ ብቻም ሳይሆን ዓለምአቀፍ መልክ ይዞ ከመንግሥት ጋር ግብግብ ገጠመ።ብዙ ተማሪዎች የሞትና የመቁሰል እንዲሁም የመታሰር ጽዋ ደረሳቸው።ብዙዎቹም ተሰደዱ።

የንጉሥ ሃይለሥላሴ መንግሥት ያገሪቱን ችግር ለመፍታት አቅም ሲሳነው፣ችግሮቹ እያደጉና እዬበዙ ሲመጡ ሕዝቡ ከዳር እስከዳር ተቃውሞ ማንሳት ጀመረ።በተለይም በድርቅ ምክንያት በደረሰው እርሃብ ምክንያት የብዙ ዜጎች ህይወት መቀጠፉና ሕዝቡ ከገጠር ወደ ከተማ እዬፈለሰ መምጣቱ በዚያ ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የነዳጅ ቀውስ ሁኔታውን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ አደረገው። አገሪቱ ከዳር እስከዳር በሕዝብ ተቃውሞ ተናጠች።ወደ ሌላ የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ከተታት።

የተማሪው እንቅስቃሴ አድጎ የፖለቲካ ቅርጽ ይዞ ለመውጣት ከአስር ዓመት በላይ ፈጅቶበታል። በኢትዮጵያዊነት ከተሰባሰቡት የፖለቲካ ድርጅቶች ጎን ለጎን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ዓላማ ይዘው ጫካ የገቡ የብሔር ነጻ አውጭ ድርጅቶችም እንደ አሸን ፈሉ።ቀደም ሲል ጫካ ከገባው የኤርትራ ነጻ አውጭ ከጀበሃ ሌላ የኤርትራ ሕዝብ ነጻ አውጭ(EPLF)ሻእብያ፣ህወሃትና ኦነግ ዋናዎቹ ናቸው።በአገር አቀፍ ደረጃ የተማሪው ትግል ማህጸን ኢሕአፓና መኢሶን የተባሉትን ግራ ዘመም የፖለቲካ ድርጅቶች ወልዶ በከተማና በገጠር ለትግል ተሰለፈ።ውሎ ሳያድር የተነሳበት አገራዊና የጋራ ችግር ተዘንግቶ በትግል አቅጣጫና መስመር ያለመግባባት ተፈጥሮ በእርስ በርስ ሽኩቻና የስልጣን ውድድር እርስ በርሱ ሲራኮት የተማሪውን የተባበረ ትግል ከሁለትና ከዚያም በላይ ከፈለው።መከፈልም ብቻ ሳይሆን እርስ በርሱ መገዳደል ያዘ።ይህ ልዩነት በንግግር ሊወገድ ሲገባው በእልህና በእብሪት ለደርግ ወታደራዊ አምባገነን የ 17 ዓመት አገዛዝ በር ከፈተለት።የኋላኋላም አንዱም ሳይተርፍ ሁለቱም የእሳት እራት ሆኑ።የተማሪው ትግል በዚሁ የቁልቁለት መንገድ ተጉዞ የሞተው ሞቶ የተረፈው የደርግ አሽከር ሆነ ሌላውም በዬአገሩ ተሰደደ።

በተማሪው ትግል ማህጸን ውስጥ የተፈጠሩት ጸረ አንድነትና ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ከውጭ ጸረ ኢትዮጵያ ከሆኑ መንግሥታትና ቡድኖች እርዳታ እያገኙ የማይበገሩ ሃይሎች ሆኑ።ከ17 ዓመት ትግልም በኋላ አረመኔውን የወታደር አምባገነን መንግሥት ለመጣል ቻሉ።አገሪቱን ተቆጣጥረው የሚፈልጉትን ማድረግ ጀመሩ።ሻእብያ የኢትዮጵያን ሕዝብ ብቻም ሳይሆን የኤርትራን ሕዝብም ፍላጎቱን በአግባቡ ሳይጠይቅ ኤርትራን ገንጥሎ ነጻ አገር አደረጋት፤ ኢትዮጵያንም የባህር በሯን አሳጣት።ትህነግ/ህወሃትና ኦነግም ለጥቂት ዓመት አብረው ከገዙ በኋላ በጥቅምና ሥልጣን ተጣልተው ኦነግ ተመልሶ ጫካ ገባ። ትህነግ/ሕወሃት ለብቻው በአምሳሉ ከቀፈቀፋቸው አጃቢ የጎሳ ድርጅቶ ጋር ሆኖ ለ27 ዓመት በሥልጣን ላይ ቆዬ።በጭካኔ አገዛዙ፣በዘረፋና ሙስና የተጨማለቀው ህወሃት በሕዝብ ትግል ከሥልጣን ወንበሩ ላይ ተወግዶ በአምሳሉ ከፈጠራቸው ሎሌዎቹ መካከል በምዕራባውያን በተለይም በአሜሪካኖች ምልመላ ሥልጣኑን ኦሕዴድ የተባለው የኦነግ የበኸር ልጅ ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሮ ሌሎቹን እንደ አባቱ ሕወሃት አጃቢ አድርጎ አገር ማተራመስ፣መዝረፍ፣ማፈናቀሉን ተያያዘው። በኢትዮጵያዊነታቸው የማይደራደሩትን ማህበረሰቦች በተለይም በአማራውና የኢትዮጵያዊነት እሴቶች ናቸው በሚላቸው ተቋማት ላይ ግልጽ ጦርነት ከፍቶ በማውደም የጭካኔና የጥላቻን ክብረወሰን የሰበረ አረመኔ መሆኑን በግልጽ አሳዬ።ገና ያልተወለደ በማህጸን ውስጥ የተኛን የሰው ልጅ ጽንስ ሆድ ቀዶ አውጥቶ በመጣል የዓለማችን የዘመኑ ጨካኝ ፍጡር መሆኑን በአደባባይ አስመሰከረ። አሁንም እዬዘረፈ፣እዬገደለ፣ኢትዮጵያንም ለመበታተንና ሕዝብንም እርስ በርሱ ለማጫረስ ተግቶ እዬሰራ ነው። በግርግር የያዘውን ሥልጣን የዓላማው ማስፈጸሚያ አድርጎ በመጠቀም የመገንጠል ዘላቂ ግቡን አሁን ወይም ሞት ብሎ ተነስቷል። ሕዝቡም በተለያዩ ወቅቶች እምቢተኝነቱን ቢገልጽም የድሉ ባለቤት ለመሆን አልቻለም።ለዚያ ምክንያቱ በዋናነት በውስጡ ባሉ አድርባዮች የሚከናወንበት ጸረ ሕዝብ ድርጊት እንደሆነ አይካድም።

ሕዝቡን እስከዛሬ ድረስ ላለፉት የመከራ ዘመናት የዳረገው ሌላው ተጨማሪ ዋና ምክንያት ትግል ሳያደርግ ቀርቶ ሳይሆን የሚታገልበትን ምክንያቱንና ዓላማውን በቅጡ ተረድቶ የሚመራው ድርጅት ባለመኖሩ ነው።በአሁኑ ጊዜ ከዬትኛውም ጊዜ በበለጠ ከመቶ በላይ የሆኑ አላስፈላጊ “የፖለቲካ ድርጅቶች” አሉ።ወጉ አይቀር!አብዛኛዎቹ በጎሳ ማንነት ዙሪያ የተደራጁና በአገር አቀፍ ደረጃ ስም ብቻ ሆነው የቀሩ የኦሕዴድ አጃቢና ስርዓቱን ተቀብለው ከባለተረኛው ድርጅት ኦነግ ኦሕዴድ ዳረጎት የሚቀበሉና የሚመራበትንም አገር አፍራሽ ሕዝብ አጫራሽ የሆነውን ሕገ ጥፋት የተቀበሉ አድርባዮች ብቻም ሳይሆኑ አገር ስትፈርስ የድርሻቸውን ቦጭቀው የመንደር ነገሥታት ለመሆን ቋምጠው የተቀመጡ ጅሎች  በመብዛታቸው ነው።አገር በነዚህ አይነቶቹ መዳፍ ስር በመውደቋ የነገው ተስፋዋ የጨለመ ሆኗል።ተስፋዋ ብሩህ እንዲሆንና ከወደቀችበት አዘቅት ወጥታ ትንሳኤዋን እንድታበስር በሕዝቡ ስም የሚነግዱትን ሕጋዊ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ከስርዓቱ ነጥሎ ማዬት አይገባም።የትግሉ አጋር ይሆናሉ ብሎ ማሰብም ጅልነት ነው።ካለነዚህ ሽፋን ሰጭነት ስርዓቱ እርቃኑን ይቀር ነበር።

አሁን የተነሳሳው ሕዝባዊ አመጽ እንዳለፉት ሕዝባዊ ትግሎች መና ሆኖ እንዳይቀር  መጠንከርና ማደግ አለበት።ለዚያም ትግሉን የሚመራ አንድ ግዙፍ ሕዝባዊ ድርጅት ሊኖር ይገባል።እስከአሁን ድረስ በዬቦታው በተለይም በአማራው ማህበረሰብ በኩል የተቀሰቀሰው እምቢ ባይነት ከግለሰቦች አመራር ወጥቶ ድርጅታዊ ቅርጽ ያለው አመራር እንዲኖረው ካልሆነ ውጤቱ ላለፉት ብዙ ዓመታት ከተደረገው ትግል የተለዬ አይሆንም።

እርግጥ ነው የግለሰቦች ሚና መናቅና መኮሰስ የለበትም፤ይህ ማለት ግን ድርጅትን ተክተው ለዘላቂው ድል ያበቁታል ማለት አይደለም።ይበልጥ ውጤታማ ሥራ ሊሰሩ የሚችሉት በድርጅት ውስጥ ሲካተቱና በችሎታቸው መጠን ተመድበው ሲሠሩ ብቻ ነው።ትግል ባለብዙ ዘርፍ ነው።ያንን ሁሉ ዘርፍ ድርጅት ካልሆነ በቀር ግለሰቦች ሊሸከሙት አይችሉም።በዓላማ ጥራትና በመርሃ ግብር፣ በፍልስፍና ፍኖተካርታ የታገዘ ፣ብዙሃንን ያሳተፈ አመራር የሌለው እንቅስቃሴ ለግለሰቦች ውድድርና የእርስ በርስ ንትርክ ይጋለጣል፤ትግሉንም ይጎዳል።መሪ ግለሰብ ቢሞት ወይም ባልታወቀ ምክንያት ከትግል ሜዳ ቢሰወር ጭፍራው ይበተናል።ድርጅት ከሆነ ግን አንዱ በሌላው እዬተተካ እስከድል ድረስ ይዘልቃል።ለዚያም ነው ድርጅት!ድርጅት አሁንም ድርጅት የሚለው ድምጽ ጎልቶ የሚሰማው።

ይህንን በተመለከተ ላለፉት ዓመታት በውጭና በውስጥ የተደረገው ተቃውሞና ትግል፣ስብሰባና የገንዘብ መዋጮ የተፈለገውን ውጤት ላያመጣ የቻለው እምነት የሚጣልበት፣አስተማማኝ፣ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አንድ ድርጅት ባለመኖሩ ነው። በዬቦታው ቁጭ ቁጭ ያሉ በአማራው ስም የሚንቀሳቀሱ ስብስቦች በመኖራቸው ለአንድነት እንቅፋቶች ሆነዋል።አንዳንዶቹም ለግለሰቦችና ለቡድኖች ግብአትና ዝና ውለዋል፤እዬዋሉም ነው።ሌሎቹ ትግሉን ከራሳቸው ጎጥ አንጻር ስለሚመለከቱት ከሌላው ጋር ያለመሥራት በሽታ ለክፏቸዋል።በዚህ አይነቱ እኩይ ተግባር የተሰማሩት እንኳንስ ጠላትን ለመታገል  አንድ ድርጅት ለመፍጠር ይቅርና እርስ በርሳቸው ተቀራርበው ለመነጋገር አልቻሉም።

በግለሰቦችም በኩል የሚደረገው ትግል እንዲሁ ለችግር በተደጋጋሚ መጋለጡን ታዝበናል።የፋኖ መሪ የነበረው ዘመነ ካሴ በሽምግልና ስም ቀርቦ የብልጽግና እስረኛ ከሆነ ስድስት ወር አለፈው።ሰሞኑንም የምስራቅ ወሎ የፋኖ መሪ የሆነው ምሬ ወዳጆና ምክትሉ በሽምግልና ስም ተታሎ ከጠላት እጅ ውስጥ ገብቶ ጭፍራው መበታተኑ ይሰማል። ይህ ሁኔታ ካልተቀዬረና አንድ ማእከላዊ ድርጅት ካልተፈጠረ ትግሉ ውጤት አይኖረውም።ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች የሚንቀሳቀሱት በፈጠሩት ድርጅት ስር በመሆኑ ከአማራው የበለጠ ጉልበት ፈጥረዋል፤ተሰሚነትም አግኝተዋል።አማራው ከነሱ የበለጠ ድርጅት መፍጠር እዬቻለ ባለማድረጉ ተበታትኖ በዬቦታው እንደ ቁራ ጩኸት እያሰማ፣ልጆቹን በመገበር ላይ

ቀጥሎበታል።ይህ መቆም ያለበት ወሳኝ ተግባር ነው።አገር ወዳዱ ኢትዮጵያዊ በተለይም አማራው በተያዘው መንገድ መቀጠል አይኖርበትም ፤ፄት እንደገባ ለማያውቀው መዋጮም እጁን መዘርጋት የለበትም።ለማን እንደሰጠ፣ፄት ላይ እንደዋለ፣የትግሉ አቅጣጫና ግብ ምን እንደሆነና በነማን እንደሚመራ የማወቅ መብት እንዳለው መረዳት አለበት።ካለፉት ድርጊቶች ሊማር ይገባል።

አሁን የህወሃትና የኦነግ ጥምረት የምዕራባውያንን ድጋፍና ትኩረት ይዞ በአማራው ላይ ጦርነት ከፍቶበታል።በአማራው ላይ ይሁን እንጂ የዘመቻው ጉዞ ሌሎቹን የሚጎዳ ኢትዮጵያን የማፍረስ ዓላማ ያለው መሆኑ አይካድም።ኦነግ ለሚፈጥራት ኦሮሚያ የመሬት ዘረፋውን በሰፊው ቀጥሎበታል፤ ህወሃትም የወልቃይትንና የራያን ለም መሬትና መውጫ በር ካልያዘ ትግራይን ገንጥሎ ለማስተዳደር አይችልም።ስለሆነም እነዚህን የአማራውን መሬቶች መንጠቅ የሞት የሽረት ጥያቄው ነው።የሁለቱ ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች የመሬት ነጠቃ በአማራው ብቻ አይቆምም፤ በቀጣይ የሌሎቹ ጎሳዎች ተራ ይሆናል። መሆኑንም በተደጋጋሚ አይተናል።ስለሆነም ኢትዮጵያ አገሩ እንዳትፈርስበትና መሬቱን ተነጥቆ ለባርነት ኑሮ መዳረግን የማይሻ ሁሉ በአገር አድኑ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፉ የግድ ይላል።ኢትዮጵያን ማዳን እራስንም ማዳን ማለት ነው።

ኦነጋውያኑም ሆኑ ህወሃታውያን የተነሱበትን አገር ግንጠላ ለማሳካት ከአሁን የተሻለ ጊዜና ዕድል የለንም አሁን ወይም በጭራሽ ብለው ተነስተዋል።እኛም ኢትዮጵያውያን ለዘለቄታው ክብራችንና ነጻነታችን፣ለአገራችን ልዑላዊነትና እድገት አሁን ወይም በጭራሽ ብለን መነሳት ያለብን ወቅት ላይ ደርሰናል።የተበታተነውን ሃይላችንን በአንድ ድርጅት ጣራ ሥር አሰባስበንና አሰልፈን የተጀመረውን ትግል መልክ ልናስይዘው ይገባል።ይህ መነሳሳት ከተዳከመ ዳግም ለመነሳት አዳጋች ይሆናል።ብረት እንደጋለ ነውና!

በትግሉ ዙሪያ ብዙ ጭልፊቶች ስለሚኖሩም በንቃት መጠበቁ ለትግሉ ስኬት ዋስትና ነው።አይተነው ጊዜ በሚሉ ጥቅመኞች ላለመጠለፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል። ሕገጥፋቱን ተቀብለው ከስርዓቱ ጋር ተቆራኝተው የቆዩትን በሆደ ሰፊነት ማቅረብ ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም።ሁሉም እንደሥራው መፈረጅ ይኖርበታል።አርና ማር አንድ ስልቻ ውስጥ አይገባም።የትግል ጥራት ማለትም ከዚህ ጠላትና ወዳጅን ለይቶ ከማወቅ ይጀምራል።

የአገር መከላከያ የሚል ጭንብል የደፋው የኦነግ ሃይል በገዛ ሕዝቡ ላይ የሚዘምት፣አገር በባእዳን ጦር ዳር ድንበሯ ሲደፈርና ሲወረር ደንታ የማይሰጠው፣ የባእዳን ወራሪ እረዳት መሆኑን በግልጽ አሳይቷል።በዚህ ተቋም ውስጥ የሚሠራ ወታደርም ሆነ ሲቪል ከተቋሙ እራሱን በማግለል ሕዝባዊ እምቢተኝነቱን መቀላቀል ይጠበቅበታል።ለአገር መሰለፍ ማለት ይህ ነውና!

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ሆይ! በኑሮ ውድነት፣በሙብራትና በውሃ እጦት መቀጣቱ፣ቤትህ በላይህ ላይ እዬፈረሰ መፈናቀሉ ሳያንስህ ሊፈጅህ የከበበህን የኦነግ ጦር ለመቋቋም እራስህን ካላዘጋጀህና ካልመከትክ አንተም እንደሰሞኑ የፋሲካ በግ የምትታረድበት ቀኑ እሩቅ አይሆንም።ልጆችህን አሳልፈህ እዬሰጠህ በደማቸው መራመዱ ይብቃህ!የጎረቤት አገሮች ሕዝብ የትግል ወኔ ላንተም ይሁን!እስከመቼ አልቃሽና ለማኝ ሆነህ ትቀራለህ?ካለፈው ታሪክህ ተምረህ አንተም ታሪክ ሥራ!ባለፈው ታሪክ መኩራት ብቻ በቂ አይደለም፤ለአሁኑም ሆነ ለወደፊቱ ችግር መፍትሔ አይሆንም። ይዞ መገኘት እንጂ ነበረኝ ማለት አያኮራም።

መላው የሠራተኛው መደብ አባል ሆይ!ለሰብአዊና ለዜግነት መብትህ የምታደርገውን ጥያቄ በሽርፍራፊ የገንዘብ ድለላ ለመሸንገልና ተቃውሞህን ለማዳፈን መንግሥት ተብዬው አገር አጥፊ ቡድን ያሰበልህን ወጥመድ ተረዳ።ሊወረውርልህ ያሰበው የገንዘብ ጉርሻ ሊያርዱ ያሰቡትን ሰንጋ ቀልቦ ከማደለብ የተለዬ

ነው ብለህ አትሞኝ።ስለሆነም ጥያቄህ ,ኤኮኖሚ ብቻ ሳይሆን የአገርህ ህልውና ነውና አገር በማዳኑ ትግል ውስጥ በመሳተፍ የድርሻህን ተወጣ።ኑሮና ደስታ አገር ሲኖር ነውና አገር እዬፈረሰ በልቼ እኖራለሁ ብለህ አታስብ።ስለሆነም በአገርህ ላይ ያንዣበበውን የመበታተን አደጋ ተገንዝበህ ለትግል ተነስ! እምቢ በል!

የሃይማኖት አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች ሆይ! የፖለቲካ ጥያቄ ለዚያውም አገር የማፍረስና ሕዝብ የመጨረስ ሴራ በሽምግልናና በድርድር የሚፈታ የቤተሰብ ጥል አይደለም። ስለሆነም ለማድረግ የምትሞክሩት የሽምግልና ተልእኮ ለችግሩ የሚመጥን መፍትሔ እንደማይሆን ተረድታችሁ እናንተንም ለማጥፋት ከማይመለሰው አገር አጥፊ መንግሥታዊ አካል የሚሰጣችሁን የአማላጅነት ጥያቄ አትቀበሉ፤ ከቻላችሁ ለትግል የማይሰለፈውን ገዝቱ።እናንተም የትግሉ አካል ሁኑ። ጥቁር ልበስ ብላችሁ ቀሰቀሳችሁ ከሥራው የተባረረውን፣የታሠረውን፣ቤተመቅደሱን አላስደፍርም ብሎ ህይወቱን የሰጠላችሁን ምእመን አስቡ።ወንጌልን ጨብጣች ለወንጀለኛው መንግሥት መሳሪያ አትሁኑ! ለምድራዊ ድሎት አጉብድዳችሁ ሃይማኖታችሁን አታርክሱት! ምእመኑ እንዲርቅና ቤተክህነት ወና እንድትቀር ከሚያደርገው ተግባር ተቆጠቡ!የእውነት፣የፍትሕ፣የአገር ፍቅር ተምሳሌት ሁኑ!

ቀጣዩ ሥራ ምን መሆን አለበት?

1 በአገር ውስጥ ተበታትኖ የሚንቀሳቀሰው የፖለቲካ ልሂቅ፣የፋኖና ልዩሃይል አባል ፣ጋዜጠኛ፣የሕግ ባለሞያ፣የህክምና ባለሙያ፣የሠራተኛው መደብ አባል፣መምህራን፣ተማሪ፣የሙብት ተከራካሪ፣የእምነት ተከታዬች፣ወዘተ ዓላማውን በግልጽ ያስቀመጠ፣የወታደራዊና የፖለቲካ እንዲሁም የማህበራዊ ዘርፎችን ተግባራት በመዋቅር ደረጃ ዘርግቶ ለመንቀሳቀስ በአንድ ብሔራዊ ድርጅት ማሰባሰብ አለበት።ይህ የስርዓቱ ደጋፊና ባለሥልጣን ያልሆነና ከብልጽግና ጋር በዚህም ሆነ በሌላ መልኩ ንክኪ የሌለው መሆን አለበት።

2 በውጭ የሚንቀሳቀሰው አገር ወዳድ በአገርቤት ከተፈጠረው ድርጅት ጋር ተሳስሮ የሚጠበቅበትን ለማበርከት በመጀመሪያ የተበታተነ ሃይሉን ማሰባሰብና በአንድ ድርጅት ስር መንቀሳቀስ፣የሚያደርገውን የገንዘብም ሆነ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ አስተዋጽኦ የሚያቀናጅ ተጠሪነትና ግልጽነት ያለው አካል መፍጠር።

3 የሚዲያ ሥራ ጠቃሚነቱ ታውቆ ለትግሉ የቆመ፣ በቦርድ የሚመራ አንድ የሚዲያ ተቋም መፍጠር፤ ቢቻል በግለሰቦች የሚንቀሳቀሱትን ወደ አንድ ማእከል ማሰባሰብ።

የሁሉም መርህ አገር የማዳን ሆኖ ከውጭ ሃይሎች መዳፍ የጸዳ፣ከጎሳና ከእምነት ልዩነት የራቀ፣በራሱ የሚተማመን ፣በአገሩ ታሪክ የሚኮራ፣ለአገሩ አንድነትና ልዑላዊነት ጠንካራ አቋም ያለው፣የሰፈነውን ስርዓት መቃወም ብቻ ሳይሆን ለማሶገድ የቆረጠ ሊሆን ይገባል።የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም የሚሻና ለዚያ የሚታገል መሆን አለበት።

ለአንድ አገር፣ለአንድ ሕዝብ ለአንዲት ኢትዮጵያ!አንድ ሕዝባዊ ግንባር(ድርጅት)!